አፍሪካ ቲቪ

9

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

## ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

# ሱረቱ አት-ተካሡር

- (በብዛት የመፎካከር ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡ የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (8) ናቸው፡፡

**ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

- በዱንያ ውጥረት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ስለ ሞትና ምርመራ የሚያስታውስ ምዕራፍ ነው። በመሆኑም (የነጋዴዎች) ምዕራፍ በመባልም ተሰይሟል።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

- (1) እናንተ የሰው ልጆች ሆይ! በገንዘብና በልጆች ብዛት (በዚህች ዓለም ፀጋዎች) መፎካከር ከአላህ ትዕዛዝ (ጌታችሁን ከመገዛት)፤ አዘናጋችሁ።
- (2) ሞታችሁ ቀብር ውስጥ እስክትገቡ ድረስም ትዘናጋላችሁ።
  (መቃብሮችን እስከጎበኛችሁ ድረስ፤ በዚሁ ላይ ቀጠላችሁ)፡፡
  (እስከምትሞቱ ድረስ ቀጠላችሁ)፡፡

9

(3) ከዚህ ተግባራችሁ ተከልከሉ (ታቀቡ)፤ ወደፊት (ውጤቱን) ታውቃላችሁ፤

(ይህ መፎካከር ከአላህ ትዕዛዝ ሊያዘናጋችሁ አይገባም ነበር።

የዚህን መዘናጋት ውጤት ሳታውቁት አትቀሩም።)

(4) አሁንም ከዚህ ተግባራችሁ ተከልከሉ፤ ወደ ፊትም ታውቃላችሁ፤

የመዘናጋቱን ውጤት ሳታውቁት አትቀሩም።

(5) በእውነቱ እንደምትቀሰቀሱና እንደየሥራችሁ እንደምትመነዱ እርግጠኛ

ብትሆኑ ኖሮ በገንዘብና በልጆች ባልተፎካከራችሁ ነበር፡፡

(የሚጠብቃችሁን በእርግጠኝነት ብታውቁ ኖሮ ይህን

ያክል ባልተዘናጋችሁ ነበር)።

(6) በአላህ ስም እምላለሁ የትንሳኤው ቀን እሳትን ትመለከታላችሁ።

(7) አዎ! ምንም ጥርጣሬ የሌለበት ዕይታን በዓይናችሁ በብሌኑ ትመለከቷታላችሁ።

(ገሀነምን በእርግጥ ታያላችሁ፡፡ ከዚያ እርግጠኛን ማየት ታዩዋታላችሁ፤)

(8) በዚያን ቀንም አላህ የዋለላችሁን ውለታ (ጤንነት፣ ሀብት ወዘተ) ይጠይቃችኋል። (ከዚያ በድሎታችሁ ሁሉ በዚያ ቀን ትጠየቃለችሁ፡፡)



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ
(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ፋሓ")

አፍሪካ አካዳሚ

## ሱረቱ አት-ተካሡር ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- 1. ግዴታውን የማይወጡትለት ገንዘብ አደገኛነት፤
- 2. ስለ ቀብር ቅጣት መኖር ማረጋገጥ፤
- 3. ስለ ቀብር ጉብኚት አስፈላጊ መጠቆም፤
- 4. ሞቶ መነሳትና ከዚያም የስራን ዋጋ ማግኘት ያለ መሆኑን፤
- 5. አላህ ለሰጠው ውለታ ሁሉ መጠየቁ የማይቀር ሀቅ መሆኑን
- 6. በገንዘብ፣ በልጆች መፎካከር መኩራራት አደገኛ ስለመሆኑ።
- 7. ከሀዲያን በትንሳኤ ቀን እሳትን እንደሚመለከቱ።
- 8. በትንሳኤው ቀን አላህ ሰዎችን ስለ ዋለላቸው ውለታ የሚጠይቃቸው መሆኑን።
- 9. ቀብር ጊዜያዊ ማረፊያ (መኀብኛ ሀገር) እንደሆነችና በፍጥነት ወደ አኺራ መሸጋገሪያ መሆኗን።
- 10. የሰው ልጅ ለገንዘብ ያለው ውዴታ ተፈጥሯዊ ባህሪው መሆኑን እንማራለን።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com